# የ COVID-19 ክትባት አጋዥ ክትባቶች ምንድን ናቸው?

## ጽሁፍ

[የመሸጋገሪያ ሙዚቃ]

[ትረካ]

አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ከተከተበ በኋላ ይህ ሰው በዋናነት ከፍተኛ ደረጃ የ COVID-19 መከላከያ ይኖረዋል።

አዲስ የሚወጡ መረጃዎች ክትባቶቹ በከባድ የመታመም፣ ሆስፒታል የመግባትና የመሞት ስጋትን በመቀነስ እጅግ ውጤታማ ሆነው ቢቀጥሉም እንኳ የ COVID-19 ኢንፌክሽን መከላከያ በጊዜ ሂደት እንደሚቀንስ ያሳያሉ።

በክትባቱ የተገኘው የመጀመሪያው መከላከያ መቀነስ ሲጀምር የመከላከያ አቅምን ለማሳደግ እንዲረዳ አጋዥ ክትባት ተብሎ የሚጠራው ተጨማሪ ዶዝ ይሰጣል።

ይህ ተጨማሪ ዶዝ ለአንድ ሰው በበሽታ እንዳይያዝ ለመከላከል ተጨማሪ የሰውነት የበሽታ መከላከያ አቅም ያስገኛል።

ብዙ መደበኛ ክትባቶች ከፍተኛ ደረጃ መከላከያ ለማስገኘት አጋዥ ክትባቶችን ይፈልጋሉ።

ለምሳሌ፡ ሰዎች በየ10 አመታት ውስጥ የቴታነስ ክትባት መከተብ አለባቸው። ይህ አጋዥ ክትባት ይባላል። ክትባቱ መከላከያው በጊዜ ሂደት የሚቀንስ መሆኑን የምናውቅ እንደመሆኑ የበሽታ መከላከል አቅምዎን “ያግዛል”።

ስለ COVID-19 ክትባቶች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት health.mn.gov/covidvaccineን ይመልከቱ።

[የመሸጋገሪያ ሙዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

10/6/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ አቀራረብ ለማግኘት በሚከተለው ቁጥር ይደውሉ: 651-201-4989።*